በዴንቨር ኮሎራዶ

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት

ቤተ ክርስቲያን የተዘጋጀ

# ወደ

# ፊልጵስዩስ

ሜይ 2018

| አርዕስት | ማውጫ | ገፅ |
|---|---|---|
| ታሪካዊ ዳራ | | 2 |
| ቅኝት | | 2 |
| አስተዋጽኦ | | 3 |
| የአዘጋጆች መልዕክት | | 3 |
| ጥናት አንድ፡ የምስጋና ሰላምታ እና ጸሎት | | 4 |
| ጥናት ሁለት፡ የጳውሎስ እስራትና የወንጌል መስፋፋት | | 5 |
| ጥናት ሦስት ፡ የክርስቶስ ምሳሌነት | | 6 |
| ጥናት አራት፡ እንደ ብርሃን ልጆች መመላለስ | | 7 |
| ጥናት አምስት ፡ የጢሞቴዎስና የአፍሮዲጡ ሕይወት | | 8 |
| ጥናት ስድስት፡ ከሐሰተኞች /ከኃይማኖተኝነት መጠበቅ | | 9 |
| ጥናት ሰባት ፡ ወደ ግብ መገስገስ! | | 10 |
| ጥናት ስምንት፡ ህብረትን የመጠበቅና የደስተኝነት ሕይወት | | 11 |
| ጥናት ዘጠኝ፡ የወንጌል ማኅበርተኝነት | | 12 |

## ታሪካዊ ዳራ

የፊልጵስዩስ ከተማ የሰሜናዊ ግሪክ ክፍለ አገር የነበረችው መቄዶንያም ዋና ከተማ የነበረች ሲሆን የምትጠራውም በታላቁ እስክንድር አባት በመቄዶንያው ንጉስ በዳግማዊ ፊልጶስ ስም ነበር። የሐዋርያው ጳውሎስ በነበረበት ዘመን ፊልጵስዩስ የሮም ቅኝ ግዛት ስለነበረች የታወቀችና ብዙ የሮም ዜጎችና ወታደሮች በዚያ ይኖሩ ነበር(የሐ16:12) ።

የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተችው በጳውሎስና አብረው ያገለግሉ በነበሩት ሲላስ፣ጢሞቴዎስና ሉቃስ በሚገኙበት ቡድን ሲሆን የሐዋርያው ጳውሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ፊልጵስዩስ የሄደው እግዚአብሔር በጢሮአዳ ለሰጠው ራእይ ምላሽ ለመስጠት ሁለተኛውን የወንጌል ተልዕኮ ባደረገበት ወቅት ነበር ። ራእዩም አንድ የመቄዶንያ ሰው "ወደ መቄዶንያ ተሻገርና እርዳን "ብሎ ሲናገረው መመልከቱ ነበር (የሐዋ 16:9-40) ።

በሐዋርያው ዻውሎስና በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን መካከል ጠንካራ ወዳጅነት ተፈጠረ።ብዙ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኗ ለዻውሎስ የገንዘብ እርዳታ አድርጋለች፤ በኢየሩሳሌም ያሉትን ችግረኞች ለመርዳት ገንዘብ በሚያሰባስብበትም ጊዜ ይህች ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ልግስና እጅዋን ዘርግታለች (2ቆሮ11:9 ፣ ፊል4:15-16) ። በሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ወቅት ሐዋርያው ጳውሎስ የፊልጵስዩስን ቤተ ክርስቲያን ሁለት ጊዜ የጎበኘ ይመስላል (ሐዋ 20:1-6) ።

የሐዋርያው ጳውሎስ ሦስቱ የወንጌል ተልዕኮ ጉዞዎች በመባል የሚታወቁት የሚከተሉት ናቸው:

- የመጀመሪያው /Paul's 1st **Missionary Journey**/ ከአንጾኪያ (ሐዋ13:1-4)
- ሁለተኛው/ **Paul's 2nd Missionary Journey**//ከአንጾኪያ (ሐዋ15:36-18:22)
- ሦስተኛው/Paul's 3rd **Missionary Journey**/ከአንጾኪያ (ሐዋ18:23-20:38)

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ይህን መልዕክት ከ 60-61 ዓ. ም ገደማ በመጀመሪያው በሮም እስር ቤት እያለ ለፊልጵስዩስ ሰዎች እንደጻፈ ያምናሉ።እነዚህ ሊቃውንት ጳውሎስ በዚሁ እስር ላይ እያለ ለኤፌሶንና ለቆላስይያስ ሰዎች እንዲሁም ለፊልሞና እንደጻፈ ያምናሉ።

## ቅኝት

ከብዙዎቹ የጳውሎስ መልዕክቶች በተለየ ሁኔታ ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች የተላከው መልዕክት የተጻፈው በቤተ ክርስቲያኗ ችግር ወይም ግጭት ተፈጥሮ አይደለም። የተጻፈበት መሠረታዊ ምክንያት የቤተ ክርስቲያኒቱ ምዕመናን ለወንጌል ስራና ለጳውሎስ ላሳዩት ፍቅር ልባዊ ምስጋናውን ለመግለጽ ፣የክርስቲያን የመኖር ዓላማና የዘላለም ሕይወት ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን በመግለጽ እርሱን ማወቅ ደግሞ ከሁሉም የሚበልጥ ጥቅም ያለው መሆኑን አውቀው ይተጉ ዘንድ ለማበረታታት ነው። ለዚህም የክርስቶስን ፈለግ በመከተል በትሕትና ፣ በአንድነትና በሰላም ጌታን እንንዲያገለግሉና የደስታቸውንም መሠረት እርሱን እንዲያደርጉ ለማበረታታትም ነው።በተጨማሪም ዻውሎስ ይህን መልዕክት የጻፈው በእስራቱ ሁሉ የእግዚአብሔር ዐላማ እንዲፈጸም ለቤተ ክርስቲያኒቱ ምዕመናን ለማረጋገጥ ነው (ፊል1:12-30) ።

## አስተዋጽኦ

### ሀ. መግቢያ (1:1-26)

1. የምስጋና ሰላምታ እና ጸሎት (1:1-11)
2. የጳውሎስ እስራትና የወንጌል መስፋፋት (1:12-26)

### ለ. ምክር (1:27-2:18)

3. የክርስቶስን ምሳሌነት ስለ መከተል የተሰጠ ምክር ((1:27-2:11)
4. እንደ ብርሃን ልጆች ስለ መመላለስ የተሰጠ ምክር(2:12-18)

### ሐ. የዻውሎስ የጉዞ እቅድና ማስጠንቀቂያ (2:19-3:21)

5. የጳውሎስ የጉብኝት እቅድና የጢምቴዎስና የአፍሮዲጡ ህይወት (2:19-30)
6. ከሐሰተኞች ስለ መጠበቅ የተሰጠ ምክር (3:1-11)
7. ወደ ግብ ስለ መገስገስ (3:12-21)

### መ. ማጠቃለያ ማስታወሻ (4:1-23)

8. ህብረትን ስለ መጠበቅና ስለ ደስተኝነት ሕይወት የተሰጠ ምክር (4:1-9)

9. የፊልጵስዩስ አማኞች ለዻውሎስ ያደርጉለት ስጦታ (4:10-23)

## የአዘጋጆች መልዕክት

የተወደዳችሁ ቅዱሳን የጌታ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ!

ቃሉ ትናንትና፣ ዛሬ፣ ለዘላለምም ያው ነው። ሰማይና ምድር ያልፋሉ እንጂ እርሱ አያልፍም። እኛን ይለውጥናል እንጂ የእግዚአብሔር ቃል መቼም ቢሆን መቼም አይሻሻልም፤አይለወጥም። የፊሊጵስዩስ መጽሐፍ ልዩ ልዩ አቀራረቦች እንዳሉት ይታወቃል። እኛም ከልዩ ልዩ መርጃ መጻሕፍት በማሰባሰም የመልዕክቱ ይዘት እንደተጠበቀ ሆኖ ለጥናታችን እንዲያመች በማሰብ ከላይ እንደተዋቀረው ሆኖ አቅርበነዋል።

በዚሁ አጋጣሚ በቤተ ክርስቲያናችን ለበርካታ አመታት እየተካሄዱ ባሉ የቤት ለቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች በቋሚነት በመሳተፍ የጥናት አቀራረባችንን እንድናሻሻል ገንቢ አስተያየታችሁን ለሰጣችሁንና ለምትጸልዩልን ሁሉ ጌታ ይባርካችሁ ልንል እንወዳለን። ከእንግዲህም ቢሆን በጸጋው ይበልጥ እንድንተጋና አቀራረባችንን እንድናሳድግ እንድትጸልዩልንና ገንቢ አስተያየታችሁን ሳትቆጠቡ እንድትሰጡን በትሕትና እንጠይቃለን።

**መልካም ጥናት!**

# ጥናት አንድ: የምስጋና ሰላምታ እና ጸሎት

## የጥናት ክፍል ፡- ፊል 1፡1 – 11

**መግቢያ፡-** ሐዋርያው ጳውሎስ በሮም እስር ቤት ሆኖ ሁልጊዜ ስለ እርሱ ለሚያስቡለትና ለሚረዱት የፊልጵስዮስ አማኞች ሰላምታ ሲልክላቸው ፣ ከእርሱ ጋር በወንጌል ስራ አብረውት ስለቆሙ እንዴት በደስታ ጸሎት እንዲሚያስባቸውና በክርስቶስ ቀን ደግም እንዲገኙበት ስለሚፈልገው መንፈሳዊ አቋም ሲነግራቸው እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. መልዕክቱ የተጻፈው ለማን ነበር? ጸሐፊው ስለ ራሱና አብሮት ስለነበረው ሰው የገለጸው ምን በማለት ነበር?
2. ጳውሎስ እነዚህን አማኞች የሚያመሰግንበት ምክንያት ምን ነበር? በአካል አንድ ላይ መሆንና በክርስቶስ ስራ አብሮ መጠመድ ልዩነቱ ምንድር ነው?
3. በፊልጵስዮስ አማኞች ህይወት የተጀመረው መልካም ሥራ ምንድን ነው? ሥራውስ የሚጠናቀቀው መቼ ነው?
4. ጳውሎስ የሚጸልይላቸው በምን ጉዳይ ነው (ቁ. 9 – 11)?
5. ከቁ 9 – 11 የእግዚአብሔር ፍቅር ማደግና መብዛት ያለበት ለምንድን ነው? እንዴትስ ሊበዛ ይችላል?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. የእግዚአብሄር ልጅ ከመሆንህ/ሽ የተነሳ በህይወትህ/ሽ ውስጥ ሌሎችን የሚያሳርፍ የጽድቅ ፍሬ መታየት እንደሚገባው ምን ያህል ይታያል? ይህ እንዲባዛስ ምን ውሳኔ አደረግህ/ሽ?
7. የተቸገሩ (በችግር ላይ ያሉ) ሰዎች ስለ እናንተ/ቺ ሲያስቡ ስለእናንተ/ቺ እግዚአብሄርን የሚያመሰግኑ ይመስልሃል/ሻል?

**ማጠቃለያ**

ከክርስቶስ የተቀበልነው ህይወት የሚያድግና የጽድቅ ፍሬ የሚያፈራ መሆኑን ተገንዝበን በየዕለቱ ከጌታ ጋር በመጣበቅ (ዮሐ 15፡4–5) ለእግዚአብሄር ክብርና ምስጋና ፣ ለእግዚአብሄር እና ለሰዎች የሚሆንን ፈሬ ለማፍራት ህይወታችንን መስጠት ይጠበቅብናል (ዮሐ 15:16)።

**በቃል የሚጠና**

“በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና”ፊል1:6

# ጥናት ሁለት: የጳውሎስ እስራትና የወንጌል መስፋፋት

## የጥናት ክፍል ፡- ፊል 1 ፡ 12 –26

***መግቢያ ፡-***ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ በሮም እስር ቤት ሆኖ ሁልጊዜ ስለ እርሱ ለሚያስቡለትና ለሚረዱት የፊልጵስዮስ አማኞች ሰላምታ ሲልክላቸው ፣ ከእርሱ ጋር በወንጌል ስራ አብረውት ስለቆሙ እንዴት በደስታ ጸሎት እንዲሚያስባቸውና በክርስቶስ ቀን ደግም እንዲገኙበት ስለሚፈልገው መንፈሳዊ አቋም ሲነግራቸው ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ሐዋርያው ካለበት ከራሱ ሁኔታ በላይ የክርስቶስ ወንጌል ለእርሱ ተቀዳሚ ነገር መሆኑን እናያለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በጥናቱ ክፍል እንደምንመለከተው ጳውሎስ በህይውቱ ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር ምን እንደሆነ ይናገራል። ሌሎችስ ስለ እስራቱ ምን የሚሉ ይመስልሃል/ሻል?
2. ጳውሎስ "ስለዚህም እስራቴ" ሲል ለፊልጵስዎስ ሰዎች ፅፎ ደብዳቤ በላከላቸው ጊዜ እስር ቤት ሆኖ እንደነበር ያመለክታል። ነገር ግን ጳውሎስን ማን አሳሰረው? በምን ምክንያትስ ታሰረ? እግዚአብሔር ጳውሎስ እንዲታሰር ለምን የፈቀደ ይመስልሃል/ሻል? ጳውሎስስ በእስራቶቹ ወራቶች ምን አደረገ?
3. ጳውሎስ እንደሚፈታ እርግጠኛ እንደሆነ ይናገራል ፤ ይሄም ሊሆን ይችላል ብሎ የሚያምንባቸውን ሁለት ምክንያቶች አስረዳ/ጂ።
4. በቁ. 21 "ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፥ ሞትም ጥቅም ነውና።" ሲል ጳውሎስ ኢየሱስን ለማክበር ስላለው የኑሮና የህይወት መርህ ምን ያሳይሃል/ሻል?

***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

5. ባለህበት/ባለሽበት ቦታና ሁኔታ ወንጌልን እንዳትናገር/ሪ ምን የሚያደግርህ/ሽ ነገር አለ? ይሄስ በህይወትህ/ሽ ውስጥ ተቀዳሚ ስለሆነው ነገር ምን ያሳይሃል/ሻል?
6. ከዚህ የተነሳ  ክርስቶስ በሕይወትህ/ሽ ተቀዳሚ እንዲሆን ምን መለወጥ ያለብህ/ሽ ነገር እንዳለ ታስባለህ/ለሽ?

***ማጠቃለያ***

በሕይወትና በኑሮ ጎዳና በተለያዩ ሆኔታዎች ውስጥ ራሳችንን ልናገኝ እንችላለን። ለእኛ የማይመች ሁኔታ ውስጥ እንኳን ብንሆን ፤ እግዚአብሔር ከነገራችን ሁሉ ውስጥ ለክብሩ የሚሆን መልካም ነገር እንደሚያወጣ በመማን ራሳችንን ለእግዚአብሔር መስጠትን እንድንማር ይረዳናል።

**በቃል የሚጠና**

"ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፥ ሞትም ጥቅም ነውና።" ፊል 1:21

# ጥናት ሦስት : የክርስቶስ ምሳሌነት

## የጥናት ክፍል ፦ ፊል 1:27 – 2:11

***መግቢያ*** **፦** ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ ካለበት ሁኔታ በላይ ለክርስቶስ ወንጌል የሰጠውን ተቀዳሚነት ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ይህንኑ ወንጌል እንዲሮጥ ለማድረግ ለፊልጵስዮስ ሰዎች ከልዩነቶቻቸው በላይ ሊኖራቸው የሚገባውን አንድነት እና የክርስቶስን ምሳሌነት እንዲከተሉ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲመክራቸው እንመለከታለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁ. 1:27 – 30 ለክርስቶስ ወንጌል የተገባ ኑሮ እንዲኖሩ ሲነግራቸው እናያለን። በክፍሉ ውስጥ ለወንጌል የተገባና ያልተገባ ኑሮ ምን እንደሆነ አብራራ/ሪ።
2. ሰዎች በመከራ ውስጥ ሲያልፉ ብዙ ጊዜ ምን ማድረግ ይቀላቸዋል? በቁ 2:1 በመከራ ለሚያልፉ ወገኖች ምን እንዳለ ይገልጻል? ይሄ ለአንተ/ለአንቺ ምን ማለት እንደሆነ ትረዳለህ/ትረጃለሽ?
3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ2:1 ያለውን ሃሳብ እንዴት እንደፈጸመው (ፈጽሞታልን) አብራራ/ሪ?
4. በቁ. 2:5 ላይ "በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ" ተብሎ የተገለጸው ምን ነበር? ኢየሱስ ከአባቱ ጋር የነበረው ግንኙነትስ ?

***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

5. በልዩ ልዩ የሕይወት ሁኔታዎች ውስጥ ስናልፍ ሌሎችን እንዳናገለግልና የራሳችንን ሁኔታ ብቻ እንድናይ የሚያደርጉት ነገሮች ወይም ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
6. ዛሬ ይህ መልዕክት ለአንተ/ቺ ጥሪ የሚያቀርበው ፤ በህይወትህ/ሽ በክርስቶስ ምሳሌነት ከእነማን ጋር አብረህ/ሽ በአንድ ሀሳብ እንድትኖር/ሪ ነው? በስምምነት መኖራቹህ ለወንጌል ምን አስተዋጽኦ አለው?

***ማጠቃለያ***

በዛሬው ጥናታችን ሐዋሪያው ጳውሎስ የራሳችንን ህይወትና ጥቅም ጠባቂ ብቻ ሳንሆን ለሌሎች ቅድሚያ በመስጠት ፤ ለፍቅርና ለሕብረት የክርስቶስን ምሳሌ እንድንከተል ጥሪ ያቀርብልናል።

***በቃል የሚጠና***

"በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን።" ፊል 2:5

## ጥናት አራት: እንደ ብርሃን ልጆች መመላለስ

## የጥናት ክፍል ፡- ፊል 2:12 – 18

***መግቢያ፡-*** ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌል እንዲሮጥ ለማድረግ የፊልጵስዮስ ሰዎች ከልዩነቶቻቸው በላይ ሊኖራቸው የሚገባውን አንድነት እና የክርስቶስን ምሳሌነት እንዲከተሉ ሲመክራቸው ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በጌታችን በመድሀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በሆነ ዳግም ልደት የልጅነት ስልጣን ያገኘን ክርስቲያኖች በዚህ የጨለማ ድባብ በዋጠው ዓለም እንደ ብርሃን ልጆች እንዴት ልንኖር እንደሚገባ እናያለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ይህ ዓለም ስለምን በጨለማ የተያዘ ነው ልንል ቻልን? እኛስ ከምን የተነሳ የብርሃን ልጆች ልንባል በቃን?
2. መታዘዛችን ለታይታ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ህልውና በማሰብ ፣ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ እንዲሆን የተመከርነው ከምን የተነሳ ነው?
3. የእግዚአብሔርን ቃል ሳናጉረመርምና ሳናመነታ እንድንታዘዘው የተሰጠን መመሪያ በዚህ ድህረ ዘመናዊነት በገነነበት ዘመን (ለክረስትያኖች) ምን ያህል ጠቃሚ ነው ትላላህ?
4. በዓለም ላይ እንደከዋክብት ልናበራ የምንችለው ከምን የተነሳና ፣ እንዴት ሆነን ብንመላለስ እንደሆነ ግለጽ።
5. በእግዚአብሔር ድንቅ ስራ ሀሴትን ማድረግ ለክርስቲያን ህይወት ምን ያህል ተገቢ ነው ትላለህ? ጥቅሞቹስ?

***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

6. የዚህችን ዓለም የጨለማ ጉልበት ለመስበር የእግዚአብሔር መስማት ብቻ ሳይሆን በሕይወታችን እርሱን መታዘዛችንና መከተላችን በግል ህይወታችንና በአካባቢያችን ላይ ሊፈጥር የሚችለውን ለውጥ በማብራራት ያለህን የህይወት ተሞክሮህን/ሽን አካፍል/ዪ።

***ማጠቃለያ***

የዚህ ዓለም ገዢ ሰይጣን የተባለው ዲያቢሎስ ነው ፤ እርሱም የዚህችን ዓለም ክፋት በመሳሪያነት እየተጠቀመና እያሳተ ብዙዎችን እርሱ ወደ ሚጣልበት እሳት ለመጣል የጨለማ ድባብ አጥልቶአል። እኛ የህይወትን ብርሃን የተቀበልን ሁሉ ጨለማን እየገለጥን በእስራት ያሉትን ነጻ ልናወጣ ተጠርተናል። ብርሃን ባለበት የጨለማ ጉልበት ድል የተነሳ በመሆኑ በቃልና በስራ እንደብርሃን ልጆች እየተመላለስን የብርሃን አባት የሆነውን አምላካችንን ልናስከብር ይገባናል።

**በቃል የሚጠና**

"ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።" ፊል 2:13

# ጥናት አምስት : የጢሞቴዎስና የአፍሮዲጡ ህይወት

## የጥናት ክፍል ፦ ፊል 2፡ 19 – 30

***መግቢያ ፦*** ባለፈው ጥናት በጌታችን በመድህኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በሆነ ዳግም ልደት የልጅነት ስልጣን ያገኘን ክርስቲያኖች በዚህ የጨለማ ድባብ በዋጠው ዓለም እንደ ብርሃን ልጆች እንዴት ልንኖር እንደሚገባ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ስናገለግል ምን አይነት ባህሪያት ሊኖሩን እንደሚገባ ሐዋርያው ጳውሎስ የመሰከረላቸውን የጢሞትዮስንና የአፍሮዲጡን ህይወት በመመለከት እንማራለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ሐዋሪያው ጳውሎስ ቁ.19 "ነገር ግን ኑሮአችሁን ሳውቅ እኔ ደግሞ ደስ እንዲለኝ" እያለ የሚናገረው ፤ በፊልጵስዎስ ስላለችው ቤተክርስቲያን ምን ማወቅ ስለፈለገ ይመስልሀል/ሻል?
2. ስለ እግዚአብሔር ህዝብ ከልብ የሚገደውና የራሱን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለመፈጸም የሚሮጥ አገልጋይ ፤ ህይወቱ ምን ይመስላል?
3. እንደጢምቴዎስ ያሉ እውነተኛ አገልጋዮች በህይወት ምስክርነታቸውና በተቀደሰው አገልግሎታቸው በቤተክርስቲያን ውስጥ ሊፈጥሩ የሚችሉትን በጎ ተጽእኖ ግለጽ/ግለጪ።
4. አፍሮዲጡ ለአገልግሎት በሄደበት ቦታ እስከሞት አፋፍ ድረስ በጠና መታመሙን ስታይ በአገልግሎት ጎዳና ስለሚገጥመው ህመም ፣ ችግር ፣ መከራ እንዲሁም በጽናት ስለመቆምና ከእግዚአብሔር እጅ ምህረትን ስለመቀበል ፤ ለህይወትህ/ሽ ምን ትምህርት ቅረልህ/ሽ?

***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

5. በእግዚአብሔርና በሰው ፊት በመንፈሳዊ ህይወት ማደጋጋችንን ሰዎች ሲያዩና ሲሰሙ ሊፈጥርባቸው የሚችለውን ደስታና መበረታታት ስታይ ምስክረነቱ ምን ያህል ጠቃሚ ነው ብለህ ታስባለህ/ታስቢያለሽ?
6. በእግዚአብሔር መንግስት ጥቂቶች ብቻ እንዲያገለገሉ ሳይሆን የዘላለም ህይወት ወራሾች እንድንሆን የተጠራን ሰዎች ሁሉ ድርሻ መሆኑን ተገንዝበህ/ሽ የዳንበትን ወንጌል በምን ዓይነት መልኩ እንደመሰከርክ/ሽ ግለጽ።

***ማጠቃለያ***

እኛም እንደ ጳውሎስ አፍሮዲጡና ጢሞቲዎስ በወንጌል ሰንሰለት ተያይዘን ከክርስቶስ የተቀበልነውን ህይወት ሌሎችም እንዲያገኙት መንገዱን እንድናሳውቅ በአገልግሎት ቁርጠኝነትንና ትጋትን እያሳየን ፣ለሌሎች የፍቅር ዋጋ እየከፈልን በደስታም ሆነ በሀዘን ፣ በተድላም ሆነ በህመም ፤ በእምነት ጸንተን በመቆም የወንጌልን የምስራች እስከምድር ዳርቻ ልናደርስ ታዘናልና በግላችን በጸጋው እንበርታና እርስ በእርስም እንበረታታ ።

**በቃል የሚጠና** "እንግዲህ በሙሉ ደስታ በጌታ ተቀበሉት፥ እርሱን የሚመስሉትንም አክብሩአቸው" ፊል 2:29

## ጥናት ስድስት: ከሐሰተኞች /ከኃይማኖተኝነት መጠበቅ

**የጥናት ክፍል ፡- ፊል 3:1 – 11**

***መግቢያ፡-*** ባለፈው ጥናት በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ስናገለግል ምን አይነት ባህሪያት ሊኖሩን እንደሚገባ ሐዋርያው ጳውሎስ የመሰከረላቸውን የጢሞትዮስንና የአፍሮዲጡን ህይወት ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ እውነተኛ የሆነውን እምነታችንን እንድንይዝና ከሐሰት አስተማሪዎች ወይም አስመሳይ ከሆነ የሀይማኖተኝነት ህይወት መጠበቅ ተገቢ እንድሆነ እንመለከታለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በእግዚአብሔር ላይ ካለን እውነተኛ እምነት የተነሳ ሐዋርያው ጳውሎስ "በጌታ ደስ ይበላችሁ" ሲለን ፤ የደስታችን ምንጭ የሆኑትን አበይት ሀሳቦች ግለጽ/ጪ።
2. ሐዋሪያው ጳውሎስ "…ተጠበቁ" እያለ የሚያስጠነቅቃቸው ባህሪያት ምንድን ናቸው? በመንፈሳዊ ህይወታችን ውስጥ የሚፈጥሩት አሉታዊ (አፍራሽ) ተጽዕኖ ምንድን ነው?
3. በቁ.7 "ነገር ግን ለእኔ ረብ የነበረውን ሁሉ ስለ ክርስቶስ እንደ ጉዳት ቈጥሬዋለሁ።" ብሎ ሐዋሪያው ጳውሎስ የተናገረው ስለምንድር ነው? ለምንስ የማይጠቅሙ አድርጎ ቆጠራቸው?
4. ጳውሎስ 'የእግዚአብሔር ጽድቅ ህግን በመጠበቅ የሚገለጽ ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ባለ እምነት ነው' ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. በቁ. 10 – 11 "እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፥ በመከራውም እንድካፈል፥ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፥ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ።" ሲል ሐዋርያው ምን ማለቱ እንደሆነ በዝርዝር አብራራ/ሪ?

***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***

6. በእውነተኛ እምነትና በመንፈስ እግዚአብሔርን ማምለክና ፣ በአስመሳይ የሀይማኖተኝነት ህይወት መመላለስ ፤ ልዩነታቸውን ካለፍከባቸው/ካለፍሽባቸው የህይወት ተሞክሮዎች ጋር በማዛመድ አስረዳ/ጂ።

***ማጠቃለያ***

ትምክህታችን ስለእኛ ሀጢያት ነፍሱን በሰጠው በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በጽድቅ የምንመላለሰው የዘላለምን ህይወት እንዲያው በጸጋው ስለተቀበልን እንጂ ጽድቅን ለመፈጸም አይደለም። ክርስቶስ ኢየሱስን ለብሰን ከሰዎች ልማዳዊ ወግና አስመሳይነት ተጠብቀን ፤ የእምነታችንን መሰረት አጥብቀን እንያዝ።

**በቃል የሚጠና**

"እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፥ በመከራውም እንድካፈል፥ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፥ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ።" ፊል 3፡10 – 11

## ጥናት ሰባት : ወደ ግብ መገስገስ!

**የጥናት ክፍል ፡- ፊል 3:12 – 21**

**መግቢያ፡-** ባለፈው ጥናት እውነተኛ የሆነውን እምነታችንን እንድንይዝና ከሐሰተኞች ወይም አስመሳይ ከሆነ የሀይማኖተኝነት ህይወት መጠበቅ ተገቢ እንድሆነ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ እምነታችን ግብ ያለው መሆኑንና እንዴትስ ህይወታችንን እንዴት በዓላማ መምራት እንዳለብንና ከዚህም የሚገኘው ብድራት ምን እንደሆነ እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በቁ. 12 እና 13 ላይ ሐዋሪያው ጳውሎስ በወቅቱ የነበረበትን ወይንም የደረሰበትን የህይወት ልምምድ በተለይም መንፈሳዊ እውቀት እንዲንቀው ያደረገው ምን ይመስላችኋል?
2. ከቁ. 12 – 14 ሐዋርያው ወደፊት ለመያዝ የሚፈጥነውና የሚዘረጋው ወዴት ለመድረስ ነው?
3. በእነዚህ ክፍሎች መሰረት ሐዋሪያው ጳውሎስ የህይወቱ አላማና ወደዚያም ለመድረስ የሚሮጠው ሩጫ ምን ይመስል ነበር? ከሚከተሉት ጥቅሶች ጋር በማዛመድ ይመልሱ (1 ቆሮ 9:24 – 27)
4. በቁ. 17 ላይ ጳውሎስ "እኔን የምትመስሉ ሁኑ" ብሎ ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው? ጳውሎስ ምን አይነት ሰው ነበር? (ፊል 4:9 ፣ 1 ቆሮ 4:16 )
5. በቁ. 16 ላይ "ሆኖም በደረስንበት በዚያ እንመላለስ።" ሲል ሐዋሪያው ምን ማለቱ ነው? ጌታን ካወቅንበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን የደረስንበት እውቀት እንደ እግዚአብሔር ሀሳብ ለመኖር በቂ ነውን? ተወያዩበት።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. ብዙውን ጊዜ በህይወታችን ያለፉ መልካምም ሆኑ መጥፎ አጋጣሚዎቻችንና ልምምዶቻችን ወደተሻለው እና እግዚአብሔር ወዳየልን ነገር እንዳንገባ ለምን ይከለክሉናል?

**ማጠቃለያ**

ከሐዋሪያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ እንደተማርነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እያንዳንዳችንን የጠራበት አላማ ታላቅ እንደሆነ ተርድተን ፤ ወደዚያ አላማ ደግሞ ለመድረስ በትጋት ልንሮጥና በእርሱ ዘንድም ያለንን ሽልማት ልንቀበል ያስፈልጋል።

**በቃል የሚጠና**

"በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ።" ፊል 3:14

## ጥናት ስምንት: ህብረትን የመጠበቅና የደስተኝነት ሕይወት

**የጥናት ክፍል ፡-ፊል 4:1 – 9**

**መግቢያ ፡-** ባለፈው ጥናት አምላካችን እያንዳንዳችንን የጠራበትን ዓላማ ተረድተን ወደዚያ ለመድረስ በትጋት እንዴት መሮጥ እንደሚገባ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በወገኖች መካከል ያለውን የክርስቶስ መልካም ህብረት እንዴት መጠበቅ እንዳለብንና በነገር ሁሉ ደግሞ በጌታ ደስ የመሰኘትን ምስጢር እንማራለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በ ቁ.1 ላይ "ስለዚህ...እንዲሁ በጌታ ቁሙ..." ብሎ ጳውሎስ ምክሩን ከምዕራፍ 3:20 – 21 ካለው ሀሳብ ይቀጥላል። በጌታ መቆም (stand firm) ማለት ምን ማለት ነው? ለምንስ ያስፈልገናል?
   ከ 1 ቆሮ 16:13 እና ከ 1ቆሮ 15:58 ጋር አዛምዱት።
2. በቁ.2 ላይ ለተጠቀሱት ሁለት ሴቶች ጳውሎስ በአንድ ሀሳብ በጌታ እንዲስማሙ ሲመከር እናያለን ፤ በአንድ አሳብ መስማማት በአማኞች መካከል ሊሰጠው የሚችለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?
   ከ 1 ቆሮ 1:10 ፣ ሮሜ 12 ፡ 16 – 18 ካሉት ጥቅሶች ጋር በማዛመድ ተወያዩበት።
3. በቁ.4 ላይ "ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ፤ ደግሜ እላለሁ፥ ደስ ይበላችሁ።" ብሎ ጳውሎስ ሲጽፍ የነበረበት የህይወት ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? በመከራ ውስጥ እያለፉ ደስ መሰኘትስ እንዴት ይቻላል?
   ከሮሜ 8:31 ጋር በማዛመድ ተወያዩበት።
4. በቁ.8 ላይ ጳውሎስ "...አስቡ" ብሎ የዘረዘራቸው ነጥቦች ምንድር ናቸው? ለምንስ ያስፈልጉናል?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

5. በቁ.8 ላይ የተዘረዘሩት ሀሳቦች የመንፈስ ፍሬዎች እንደሆኑ ተረድተን ፤ አንድ ክርስቲያን ሊኖሩት የሚገባ ባህሪያት (Characters) መሆናቸውን ተገንዝበን ፤ እነዚህን ባህሪያት ሃብታችን ለማድረግ ምን ያህል እንተጋለን?

**ማጠቃለያ**

በቀረውስ እኛም የዴንቨር ወገኖች እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፣ ጽድቅ ያለበትን ነገር ሁሉ፣ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፣ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፣ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን እነዚህን እንድናስብ ጌታ ይርዳን ፡፡ አሜን!

**በቃል የሚጠና**

"በአንድ አሳብ በጌታ እንዲስማሙ ኤዎድያንን እመክራለሁ ሲንጤኪንንም እመክራለሁ።" ፊል4:2…" ሁል ጊዜ በጌታ ደስ ይበላች ሁ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ ፡፡" ፊል4:4

## ጥናት ዘጠኝ: የወንጌል ማኅበርተኝነት

### የጥናት ክፍል ፦ፊል 4:10 – 23

***መግቢያ ፦*** ባለፈው ጥናት  በወገኖች መካከል ያለውን የክርስቶስ መልካም ህብረት እንዴት መጠበቅ እንዳለብንና በነገር ሁሉ ደግም በጌታ ደስ የመሰኘትን ምስጢር ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የፊሊጵስዩስ  ወገኖች ለጳውሎስ በስጦታቸው  በወንጌል መከራው መካፈላቸውንና እርሱም  በምላሹ በዚህ የስንብት ማስታወሻው  ያቀረበላቸውን ምስጋና፣ ያነሳቸውን ሌሎች ነጥቦችንና የመጨረሻ የመዝጊያ ሰላምታውን እንመለከታለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በ ቁ.10 ላይ  ጳውሎስ "ስለ እኔ ልታስቡ ጀመራችሁ" የሚላቸው  የፊልጵስዩስ ወገኖች ምን ስላሰቡ ነበር ? ይህንንስ እንዴት እናውቃለን?
2. ጳውሎስ በቁ.11 ስለ ጉድለት አለልም **"የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል"**  በማለት  ከቁጥር 11-13  ደግሞ ሁለት ተቃራኒ የሕይወት ጠርዞችን  እየጠቀሰ "**ተምሬአለሁ**" በማለት  ኃይልን በሚሰጠኝ  በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ ብሎ ጽፎላቸዋል። ምን ማለቱ እንደሆነ በዘርዝር ተነጋገሩበት።
3. የፊሊጵስዩስ ወገኖች በጳውሎስ መከራ የተካፈሉት እንዴት ይመስልሃል/ሻል? ምን ያህል ጊዜስ እርዳታ አድርገውለታል?
4. በቁ 17 ላይ" ስጦታችሁን ፈላጊ አይደለሁም" ማለትና በ ቁ 18 ላይ  "ደስ የሚያሰኘውን  ስጦታችሁን .. ተቀብዬ ተሞልቼአለሁ አባባል እርስ በርሱ የሚጋጭ ሐሳብ አይመስልህም/ሽም?እንዴት?ተወያዩበት።
5. ጳውሎስ ለወንጌል በሚከፍለው መከራው የፊልጵስዩስ ወገኖች ላደረጉለት መልካም ትብብር  ሁሉ ያመጣላቸው የባርኮት ቃል ምን የሚል ነበር? ስንብቱንስ የደመደመው እንዴትነበር ?

### ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. የሐዋርያው ጳውሎስ  በሮም እስር ቤት በመከራ ሳለ ከጻፈው ደብዳቤና  የፊልጵስዩስ ወገኖች  ለጳውሎስ ካደረጉለት መልካም የወንጌል ትብብር አንጻር ስንመለከት እኛስ በዚህ ዘመን ስለ ወንጌል ምን ልናደርግ እንችላለን?

### ማጠቃለያ

የጌታ ሆኖ ጸጋ የሌለው ሰው የለም። በክርስቶስ የሆንን ሁላችን ልዩ ልዩ ዓይነት ጸጋ አለን ከእነዚህም ጸጋዎች ውስጥ አንዱ  የመስጠት ነው። ይህንን በልግስና በማድረግ ወንጌልን ልናስፋፋበት  እንችላለን ። ትልቁ ቁልፍ ነገር እኛም እንደ ጳውሎስ ኑሮዬ ይበቃኛል ክርስቶስ ያረካኛል በማለት ለወንጌል ቅድሚያ ልንሰጥ ይገባል።  ሽልማቱም ትልቅ ነው። የጌታ ጸጋ ይብዛልን። አሜን!

### በቃል የሚጠና

"የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን ፤ አሜን።" ፊል 4:23